**ኮቪድ-19 ወረርሽኝን የተመለከተ መረጃ**

**መጋቢት 30/ 2020 የታደሰ**



| |
|---|
| ጥሩ ስሜት ካልተሰማኝ የት መጠየቅ አለብኝ?<br>ከ 37.5 °c በላይ የሆነ ትኩሳት ወይም የመተንፈስ ችግር ሲሰሞት፣ ወደ ሐኪም ወይም ድንገተኛ ክፍል አይሂዱ፣ ከዚህ ይልቅ የቤተሰብ ዶክተር ይደውሉ፣ በበሽታው የመያዝ እድልን እና አደጋዎችን ለማስወገድ ፣ የጤና እንክብካቤ በርቀት ይሰጦታል |

## የቤተሰብ ዶክተር ወይም የሕፃናት ሐኪም ከሌለኝ ለማን ስልክ መደወል እችላለሁ?

- ወደ ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ለአጣዳፊ ሁኔታዎች ብቻ በነፃ ወደዚህ ቁጥር1500 ይደውሉ
- ወይም ከድንገተኛ አደጋ ቁጥሮች ወደ አንዱ ይደውሉ-112 ወይም 118

## ጣልያን የሚገኙበትን ክልል መሰረት በማድረግ ወደ ሚከተሉት ቁጥሮች ይደውሉ

- Basilicata **800 99 66 88**
- Calabria **800 76 76 76**
- Campania **800 90 96 99**
- Emilia-Romagna **800 033 033**
- Friuli-Venezia Giulia **800 500 300**
- Lazio **800 11 88 00**
- Lombardia **800 89 45 45**
- Marche **800 93 66 77**
- Piemonte **800 19 20 20 / 800 333 444**
- Provincia autonoma di Trento **800 86 73 88**
- Puglia **800 713 931**
- Sardegna **800 311 377**
- Sicilia **800 45 87 87**
- Toscana **800 55 60 60**
- Trentino-Alto Adige **800 751 751**
- Umbria **800 63 63 63**
- Val d'Aosta **800 122 121**
- Veneto **800 46 23 40**

ልዩ ችሎታ ያላቸው ኦፕሬተሮች በስልክ መልስ ይሰጡዎታል። የጤናዎ ሁኔታ እንዴት እንዳለ ለመረዳት እና እርዳታ ለመስጠት፣ መረጃ ይጠይቆታል ። ምንም እንኳን የመኖሪያ ፈቃድ ፣የግብር ኮድ ፣የመታወቂያ ካርድዎ ወይም ሌላ የማንነት ማረጋገጫ ሰነዶች ባይኖርዎትም፣ እንክብካቤ ይሰጦታል ፡ ማንም የጤና ባለሞያ የአቤቱታ (የውንጀላ) ሪፖርት አያደርጉም።

OIM UN MIGRATION



## ኮቪድ-19 በተመለከተ ጣሊያን ውስጥ ምን እየሆነ ነው?

COVID-19 ተብሎ የሚጠራው ተላላፊ በሽታ የሚያስከትለው አዲሱ ኮሮና ቫይረስ ሰው ሲያስልና ሲያስነጥስ ወይም ሲተነፍስና ሲናገር ከአፍ እና አፍንጫ በሚወጡት ነጠብጣቦች አማካይነት ከሰው ወደ ሰው ይተላለፋል።
ኮሮና ቫይረስ ማንኛውንም ዜጋ በየትኛውም ዕድሜ ክልል ላይ ያለን ሰዉ የቆዳ ቀለም ፣ ጾታ እና ሃይማኖት ሳይለይ እያንዳንዳችንን ሊበክል እና ሊያጠቃ ይችላል ።





የኮሮና ቫይረስ ተላላፊ በሽታ ያስከተለው ትልቁ ችግር እንደ፣Lombardia, Veneto, Emilia-Romagna,Piemonte,ያሉ ክልልሎች በጤና ሲስተማቸው ላይ ቀውስ (ጉዳት) አስከትሏል ነገር ግን ይህ ችግር የሙሉ ጣልያን ችግር እየሆነ ነው ። ስለዚህ ለራሳችን እና በዙሪያችን ላሉ ሰዎች ጤንነት ስንል በጣልያን መንግስት የሚሰጡትን መመሪያዎች ማክበር መሰረታዊ ጥቅም አለው። ይህም በጣልያን ክልል ሁሉ እጅግ አስፈላጊ ካልሆነ በቀር ፥የሰዎችን እንቅስቃሴ መገደብ ነው።
ይህ ድንገተኛ ሁኔታ በቁጥጥር ስር ከዋለ በኋላ እነዚህ መመሪያዎች ይቋረጣሉ። ። እነዚህ መመሪያዎች በየሳምንቱ ሊቀየሩ ስለሚችሉ፣ በቀጣይ አዳዲስ መረጃ ለማግኘት ከዚህ ስር የሚገኘውን ድህረገፅ ይጎብኙ ።

**http://www.integrazionemigranti.gov.it/Pagine/default.aspx**

እነዚህ መመሪያዎች፥ ግለሰቡ ከስር
በሚከተሉት ምክንያቶች ብቻ እንዲንቀሳቀስ ይደነግጋሉ

- አስቸኳይ እና ማራዘም የማይቻል የጤና ጉዳይ
- በሰነድ የተረጋገጠ የስራ ምክንያት
- ምግብ፣ መድሃኒት፣ ወይም ወሳኝ የሆኑ አስፈላጊ ነገሮችን ለመግዛት

እነዚህ ልዩ መመሪያዎች በሁሉም ዘንድ እንዲከበሩ ለማድረግ ፥ የህግ አስከባሪዉ አካላት እና ሃይሎች፣ የከተማ ፖሊስ ሆነው በመንገድ እና አደባባይ ፣ የሕዝብ ወይም የግል መጓጓዣ ተጠቅመው የሚንቀሳቀሱትን ይቆጣጠራሉ።



በሚያስቆሙበት ጊዜ፥ የተንቀሳቀሱበት ምክንያት ምን እንድሆነ ማስረዳት የሚችል፥ የራስን መግለጫ የያዘ ሰነድ መሙላትና መፈረም ያስፈልጋል። ይህን አይነት ሰንድ ከዚህ ታች ባለዉ ድህረገፅ ዳውንሎድ አርጎ መሙላትና አትሞ መፈረም ይቻላል ።

https://www.interno.gov.it/sites/default/files/allegati/nuovo_modello_autodichiarazione_26.03.2020_editabile.pdf



የሚሰጡት ቃል ፥ አስፈላጊ ከሆነ ምክንያት ጋር በትክክል የሚጣጣም መሆን አለበት። ምርምራ ስለሚደረግ፥ የሰጡት ቃል ውሸት ከሆነ ወይም ወሳኝ ያልሆነ አላስፈላጊ ምክንያት ከሰጡ ከ 400 እስከ 3000 ዩሮ መክፈል ይገደዳሉ።
**በኳራንቲን ያሉ ሰዎች፥ በቫይረሱ ምክንያት ከቤታቸው ወይም ከመኖሪያቸው በፍፁም እንዳይወጡ የሚለውን ክልከላ ጥሰው ከተገኙ፥ ከ3 እስከ 18 ወር እስር እና ከ500 እስከ 5000 ዩሮ እንደሚቀጡ ይጠበቃል።**



ወደ ስራ ለመሄድ ከቤትዎ ሲወጡ፥ ከቀጣሪዎ የተሰጠ የሥራ ስምሪት ውል ማረጋገጫ ይዘው ይምጡ።
በአንዳንድ ሁኔታዎች ደግሞ የአሠሪውን ወይም የሚሰሩበትን ኩባንያ እና ድርጅት ስልክ ቁጥር ይያዙ።

በጤና ምክንያት ከቤት የሚወጡ ከሆነ፥ የሐኪም የምስክር ወረቀት ወይም የሕክምና እርዳታ እንደሚያስፈልጎት የሚያሳይ ሰነድ ከርሶ ጋር መያዝ አለቦት ።



አስቤዛ ለማድረግ ከቤትዎ የሚወጡ ከሆነ፥ለቤቶ ቅርብ ወደሆነው ገቢያ ማዕከል(ሱቅ) እንዲሄዱ ይመከራል። በባለሥልጣናት ተጨማሪ ምርመራዎች ሊያጋጥሙ ስለሚችሉ ደረሰኙን ይያዙ።

ወደ ክፍት ሱቆች ሲሄዱ፣ በአንድ ሜትር ርቀት ተሰልፈው ፥ለመግባት የሚጠብቁ ሰዎች ያገኛሉ ፥በመክፈያ ቦታ ተመሳሳይ ሁኔታ ሊያጋጥም ይችላል።
እንደዚህ አይነት ሰልፎች በሆስፒታሎች፣ በጤና ጣቢያዎች እና በክልኒኮች ያጋጥማሉ።
በመግቢያው ላይ የሚገኙ ሰራተኞችን መመሪያ ሁልጊዜ ይከተሉ።
ጥርጣሬ ካለዎት መረጃ ይጠይቁ።

በመግቢያው ላይ የሚገኙ ሰራተኞችን መመሪያ ሁልጊዜ ይከተሉ።

በእርሶ እና በሰው መካከል እንዲሁም በእግር ሲጓዙ የአንድ ሜትር

ርቀት መጠበቅ ሁልጊዜ ያስታውሱ።

ካገር ወደ አገር የሚደረጉ ጉዞዎች፥ ግደባ እና መሰረዝ እያጋጠማቸው ነው። ይህም በወረርሽኙ ምክንያት በአየር መንገዶችና በቆንስላ ባለስልጣናት የሚደረግ ነው።

በዚህ ወቅት በሃይማኖታዊ ሥነ ሥርዓቶች ላይ መሳተፍ አይቻልም። እንዴት የአምልኮት አገልግሎት እንደሚያገኙ መረጃ ለማግኘት ከ አገልጋዩ ዘንድ ያረጋግጡ።

## በቤቶ ውስጥ

በቤት ያሉትን ዕቃዎች እና ገጽታዎችን በአልኮል እና በክሎሪን ነክ ያፅዱ እጆትን በተደጋጋሚ ይታጠቡ።
እስከ ዛሬ ድረስ ኮቪድ-19፥ ከሰው ወደ ቤት እንስሳ ወይም ከቤት እንስሳ ወደ ሰው እንደሚተላለፍ የሚያሳይ የሚያሳይ ምንም ማስረጃ የልም።

## በስራ ቦታ

ሥራዎ ካልተታገደ ፣ሁልጊዜ ከሌሎች ቢያንስ የ1 ሜትር ርቀት መጠበቆን ያረጋግጡ። አሠሪው ለሠራተኞቹ ጓንቶች እና ጭምብሎች በማቅረብ ዋስትና መስጠት አለበት።

OIM
UN MIGRATION

## እርዳታ ለመስጠት ምን ማድረግ ትችላለህ?
## መመሪያውን በመከተል፣ ይህንን መረጃ ለቤተሰብ እና ለጓደኞች ያስተላልፉ!



አዲሱ ኮሮና ቫይረስ:

ይህንን ሁኔታ በተሻለ መንገድ ለመሻገር ምን ማድረግ ይችላሉ?

የህ የቫይረስ ወረርሽኝ ወቅት፣ በኑሮአችን ሁሉ ያስከተለው ድንገታዊ እና መሰረታዊ የሁኑ ለውጦች ምክንያት፣ ውጥረት ፣ ግራ መጋባት ፣ ሀዘን ወይም ቁጣ ሊሰማን ይችላል።



በእነዚህ ከባድ ግዜዎች ላይ፣ የራሳችንን እና የቤተሰባችንን ጤና ለመንከባከብ በታቸለ አቅማችን  መስራት በጣም አስፈላጊ ነው። ለምሳሌ፣ ሂወታችንን በበለጠ መንገድ ለመምራት የሚያስችሉ፣ ትልልቅ እና ትንንሽ የሆኑ ምርጫወች  በማድረግ፣ ከዚህ ቀጥሎ ይህንን ጊዜ እንዴት መጋፈጥ እንዳለቦት የሚያሳዩ ምክሮች  ያገኛሉ።




- ታማኝ ምንጮችን በመጠቀም፣አዳዲስ መረጃወች ይከተሉ። አስፈላጊ የሆኑ የደህንነት ጥንቃቄ በማድረግ፣ ስለ ራሶት  ግላዊ ሁኔታ ያስቡ እና ዝግጅት ያርጉ። እርዳታ በሚያስፈልጎ ጊዜ ማንን መጥራት እና ወደ ማን መደወል እንዳለቦት የሚያሳይ ዕቅድ ያውጡ።
- ከምታምናቸው ሰዎች ጋራ  ግንኙነት ይኑርህ። በቂ እንቅልፍ እና እረፍት መውሰድን ያረጋግጡ። በቀን ውስጥ የእረፍት ግዜ ወስደው የሚወዱትን ነገር ያድርጉ።



- ሚድያ እና የብዙሃን መጋነኛ አጥቃቀም በመቀነስ ብዙ መረጃ ከመፈለግ ይቆጠቡ። ይህንን የአደጋ ግዜ ለማለፍ አስፈላጊ መረጃ  ከአገኘህ ብኋላ፣በተጨማሪ አዳዳዲስ መመርያዎችን ለመፈለግ ህጋዊ የሆኑ ድህረ ገጾች እና ታአማኝ ምንጮች፣ ለምሳሌም የጤና ጥበቃ ሚኒስተር (http://www.salute.gov.it/portale/home.html), እና የከፍተኛ የጤና ማዕከል (https://www.iss.it/)   የመሰሉትን ይጠቀሙ።።



## ህፃናቶች ይህንን ሁኔታ እንዴት መጋፈጥ እንዳለባቸው የሚያሳዩ ምክሮች



በዚህ አስቸጋሪ ሁኔታ የእርስዎ ልጆች የበለጠ ጥንቃቄ እና እንክብካቤ ያስፈልጋቸዋል። ፍቅር መስጠትን ያረጋግጡ፣ እነሱን በመዳመጥ እና በማነጋገር ደህንነት እና ድጋፍ ይስጡዋቸው። በዚህ ሁኔታ ውስጥ ምን ኢየሆነ እንዳለ እና ምን ማድረግ እንደአለባቸው እንዲያውቁ እና ተረጋግተው እንዲቆዩ አስረዳቸው። ከሁኔታው ጋር እንዲላመዱ ህጻናቶችን ለመረዳት ቀላል ቃላቶች እና የፈጥራ ምሳሌዎችንይጠቀሙ። የልጆችን ምላሽ አስተውል ደግሞ ጥሩ ምሳሌ ሁናቸው።



የጨወታ ግዜያችው እድል በመስጠት ደህንነት እንዲሰማቸው ያድርጉ። በቤት ውስጥ የሚቀምጡ ከሆኑ የጨወታ፣ ይጥናት እና የእረፍት ግዚያቶችን በመከፋፈል እንደተለመደው መደበኛ ግዜ ያድርጉት። ልጆች በመጋነኛ ብዙሃን የሚያገኙት መረጃ በደህንነታቸው ላይ ተጽኖ ሊያመጡ ይችላሉ። በዚህ ድንገተኛ ግዜ ውስጥ ለጆች ከወላጆቻቸው ወይም አብዛኛው ግዜ ከየሚንከበከባቸው ሰዎች ጋር እንዲሆኑ ይመከራል።

አንዱን ከሌላው መለያየት አስፈላጊ ከሆነ፣ መደበኛ የመገናኘት ጊዜያቸውን እና ደህንነታቸውን ያረጋግጠ መሆን አለበት።



OIM
UN MIGRATION